FROM OBLIVION TO MEMORY

# The FOM Newsletter

*Commemorating Ethiopian prisoners of the Italo-Ethiopian War*

ቅጽ 1 · ቁጥር 2 መስከረም/ጥቅምት fromobliviontomemory.org

## ከዝግጅት ክፍላችን

የዘንድሮው የአሜሪካው የጣልያን ጥናቶች ማኅበር ዓመታዊ ጉባኤውን ያካሄደው ከግንቦት 26 እስከ 28 ድረስ ሳሳሪ በምትባል የሳርዲኒያ(ጣልያን) ከተማ ውስጥ ነው። መዘክር ከሰሜን አሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች የጣልያን ጥናት ክፍሎች የተውጣጡ ምሁራን፣ ተመራማሪዎች፣ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች በተገኙበት በዚኽ የሦስት ቀናት ጥናታዊ ጉባኤ ማጠቃለያ ላይ ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ ነበር። በዚኽም መሠረት የመዘክር አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በስብሰባው ላይ ተገኝተው ንግግር አድርገዋል። አለመረጋጋት፣ እንክብካቤ እና ነፃነት ጉባኤው ያተኰረባቸው ሦስት ጭብጦች መዘክርም ትኵረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። በተለይ አለመረጋጋት፤ ቁስን ወይም ሥነ ልቡናን የሚነካ፣ የደህንነት መጥፋትን ወይም አስተማማኝነት ማጣትን የሚመለከት እንደመኾኑ መጠን፤ ከቤታቸው ከሀገራቸው በግድ ሩቅ ተወስደው የታሠሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከገጠማቸው እና ካለፉበት ኹኔታ ጋራ በእጅጉ ይመሳሰላል። በሚያሳዝን መልኩ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን ኹኔታ በሚመለከት ያለው መረጃ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ በጣልያኑ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ በአያትና ቅድመ አያቶቻችን ላይ የደረሰውን መከራ፣ በብቸኝነትና በስደት ያሳለፉትን ጊዜ እንዲኹም ትተዋቸው ስለሄዱት ልጆች እና ሌሎችም ሕይወት ለመረዳት ስለምናደርገው ጥረት እና ስለምንሠራው ሥራ ለማስረዳት ችለናል።

በግንቦቱ ጉባኤ የነበረን ሌላኛው መርሐ ግብር፤ የዛሬ ዓመት በመጀመሪያው የአዚናራ ጉዟችን ወቅት አግኝተናቸው የነበሩትን ጣልያናዊ አጋሮቻችንንና ሌሎችንም በማግኘት፤ ስለ ሥራችን ወቅታዊ መረጃዎችን ማካፈል ነበረ፡፡ በዚህም መሠረት ከአዚናራ ብሔራዊ ፓርክ አስተዳደር፣ ከሲላንድ አዚናራ አከባቢ የታሪካዊ አስጎብኚ ድርጅት፣ ከስቲንቲኖ ከንቲባ፣ ከሳሳሪ ከተማ ምክር ቤት ተወካይ እና ከሌሎችም ጋር ሰፊ ውይይት አካሄደናል፡፡ በውይይታችንም፤ ባለፈው ዓመት ካደረግነው የመጀመሪያው የአዚናራ ጉብኝታችን በኋላ በነበረው ጊዜ ውስጥ ስለ ሠራናቸው ሥራዎች፤ ማለትም፤ ሕጋዊ ዕውቅና ያለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት መመሥረታችንን፣ ስለእያንዳንዱ እስረኛ መረጃ የመዘገብ እና የሕይወት ገጽታን በትክክል ማሳየት የሚችል ድንቅ ድረ ገጽ መሥራታችንን፣ በሦስት የተለያዩ ቋንቋዎች የሚቀርቡ አራት በደንብ የተጠኑ የዜና መጽሔቶችን ማዘጋጀታችንን በመግለፅ ምን ያህል የመሥራት አቅም እንዳለን ማሳየት ችለናል። አጋሮቻችንም፤ እስካሁን ያለውን ተግባርና ጥረት ባግባቡ ተረድተው ሥራችንን በመደገፍ እ.ኤ.አ. በ1937 አዚናራ ውስጥ ታስረው ለነበሩት ኢትዮጵያውያን ቋሚ መታሰቢያ ሊቆምላቸው የሚችልበትን መድረክና ኹኔታ ለማመቻቸት ቃል ገብተውልን ተሰነባብተናል።

የመዘክር አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በዚህ አጋጣሚ፤ ለልጅ ኃይሌ ወልደ መስቀል በተዘጋጀ የመታሰቢያ ሥነ ሥርዓት ላይ የመገኘት ዕድል አግኝተዋል። ልጅ ኃይሌ ወልደ መስቀል የኤልፊ ኑቬሎን ቅድም አያት ሲኾኑ ታስረው የነበረው፣ ሕይወታቸው ያለፈውና ቀብራቸው የተፈጸመው ጣልያን ሳሳሪ ውስጥ ነው። የልጅ ኃይሌ መታሰቢያ እንዲመረቅ የተደረገው በኢጣልያ ወረራ ወቅት የተጠቃን አንድ ቤተሰብ ለመዘከር ታስቦ ሲኾን ሥነ ሥርዓቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህን ፀሎት የተመራና የአካባቢው የኢጣልያ ባለሥልጣናትም የተገኙበት ነበር።

መዘክርም በበኵሉ ከጣልያን ወረራ ጋራ በተያያዘ ለመከራ፣ ለሥቃይ፣ ለሞት እንዲኹም ለንብረት ውድመት የተዳረጉ ቤተሰቦችን በሙሉ የሚዘክር መታሰቢያ የማኖር ዕቅድ አለው። በአዚናራ ቋሚ መታሰቢያ እንዲኖር የሚደረገው ጥረትም የዚሁ ዐላማ አካል

ነው። የሳሳሪውን ጉዟችንን የሚያሳይ አጭር ቪዲዮ በዚህ ማስፈንጠሪያ ይገኛል።

## ፅሑፎች



*ቀኛዝማች ፀምሩ 1960*

### ቀኛዝማች ፀምሩና ቤተሰባቸው

ቀኛዝማች ፀምሩ ገብረ ሥላሴ ከእናታቸው ከክብርት ወይዘሮ እሴተ እና ከአባታቸው ከክቡር ፀሓፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በ1887 ደብረ ብርሃን ከተማ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም በባሕላዊው የቄስ ትምህርት ገብተው ከተማሩ በኋላ፤ ከወይዘሮ ሡናይት ወልደ ገብርኤል ጋራ ትዳር መሥርተው ዐሥራ ስድስት ልጆችን አፍርተው አሳድገዋል።

**ይቀጥላል...**

### አቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ እና ሥራዎቻቸው



*አቶ መኮንን ወልደዮሐንስ*

አቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ ከእናታቸው ከወይዘሮ ወደርየለሽ ወልደ ገብርኤል እና ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ዮሐንስ ናደው በሐምሌ 13 ቀን፣ 1897 በዐዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተወለዱ። እናታቸው ወይዘሮ ወደርየለሽ የመንዝ ተወላጅ ሲኾኑ፣ ዐዲስ አበባ ከተማ አነስተኛ ሱቅ ነበራቸው። አባታቸው አቶ ወልደ ዮሐንስ ናደው ደግሞ ኮርቻ፣ አፎት እና የተለያዩ የቆዳ ምርቶችን በመሥራት የሚታወቁ የቡልጋ ሰው ነበሩ።

**ይቀጥላል...**



*መርካቶ የሚገኘው አሜሪካን ግቢ።*

### አሜሪካን ግቢ

በ1910 አጋማሽ፣ በዘመነ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፣ መርካቶ አካባቢ አንድ የድንጋይ ሕንጻ ተገነባ። ሕንጻው የተገነባው በወቅቱ የጦር ሚኒስትር ለነበሩት ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ መኖርያ እንዲኾን ታስቦ ነው። የጦር ሚኒስትሩ ወደዚኽ መኖርያ ቤት ከመዘዋወራቸው በፊት አሁን የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የቆመበት ስፍራ ላይ የተሠራ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። የእርሳቸው አጃቢዎችም እዚያው አካባቢ ይኖሩ ስለነበረ መርካቶ ዙሪያ ሰፊ መሬትና ንብረት ነበራቸው። በርግጥ ያ በድንጋይ የተሠራና ግርማ ሞገስ ያለው ሕንጻ መኖሪያ ቤታቸው ብቻ ሳይኾን፤ ችሎት ማስቻያቸውም ነው።

**ይቀጥላል...**

# ሰሞነኛ ሁነቶች

## የድርጅታችን መጠሪያ ስም

"From Oblivion to Memory (F.O.M.)" ድርጅታችንን ወክሎ በመጠሪያነት የሚያገለግል የእንግሊዘኛ ስም እንደኾነ ይታወቃል። ከእንግሊዘኛው በተጨማሪ ድርጅታችን የዐማርኛ እና የጣልያንኛ ስም ያስፈልገው ስለነበረ፤ በዐማርኛ "መዘክር" በጣልያንኛ ደግሞ "Dall'Oblio alla Memoria" የድርጅታችን መጠሪያ ስም እንዲኾን ተወስኗል። ስያሜው ይኽ የሆነበት ምክንያት ለመጥራትም ኾነ ለማስታወስ የሚመች፣ ብሎም ዐላማውን በተወሰነ ደረጃ ሊገልፅ የሚችል ስለኾነ ነው። ከታች የምትመለከቱት ዐርማ የድርጅታችንን የዐማርኛ እና የእንግሊዘኛ ስያሜ አካትቶ የያዘ ነው።

## የጠቅላላ ስብሰባ ጥሪ

ቅዳሜ መስከረም 23 ቀን 2019 (October 3, 2026) በአዲስ አበባ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ 2 ሰዓት (1:00 p.m. Eastern time) በተዘጋጀው የአባላት፣ ደጋፊዎችና ወዳጆች ስብሰባ ላይ እንድትገኙ መዘክር በአክብሮት ይጋብዛችኋል። ይህን ጥሪ ለሌሎችም በማጋራት ተባብራችሁን ያልሰሙ ወገኖችንም ጋብዙልን። እናመሰግናለን።

## መደበኛ ስብሰባዎች

በሁለት ወር አንድ ግዜ፡- አስተባባሪ ኮሚቴ

በየወሩ፡- የጥናት፣ መዛግብትና ስነዳ ኮሚቴ፣ የፋይናንስ ኮሚቴና የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ

በየዓመቱ ፡- ጠቅላላ ስብሰባ

ቀጣይ ስብሰባዎችን ለመከታተል WhatsApp ላይ United የሚባለው ግሩፕ ላይ ያሉ መልዕክቶችን ይከታተሉ።

እኛን ለማግኘት፡- info@fromobliviontomemory.org




**ይህን ጦማርና ሌሎች ሥራቻዎችንን ለማገዝ እባክዎ በዚህ ማስፈንጠሪያ በመግባት ድጋፍ ያርጉልን።**

**ይለግሱ**

## አስተዋጽዖ አበርካቾቻችን

በዚህ በየሦስት ወሩ የሚወጣ ዝግጅታችን ሁለተኛው ዕትም ላይ ለተሳተፉትና ስማቸው ከዚህ በታች ለተጠቀሰው ሰዎች ምስጋና እናቀርባለን።

### መረጃ ለማሰባሰብ፡-

ኤደን ደበበ እና ካሌብ ደበበ።

### ለምርምር፣ ለጽሑፍ እና ለዕርማት፡-

ተስፋዬ አድኃኖም፣ አስቴር አንቶሒን፣ ጌታብቻ መኮንን፣ ላቀች

### ለትርጉም ሥራ:-

ደብሪቱ መርዕድ ካምፖሬአሊ፣ ጋብሪዬላ ጌርማንዲ ፣ ኃይሌ ከበደ፣ መቅደስ መስፍን እና አንጀሊካ ፔሳሪኒ

መኮንን፣ ኒቆዲሞስ መኮንን፣ መቅደስ
መስፍን፣ ዋሲ ተስፋ፣ ሊዲያ ተስፋዬ
እና ያድዋ የወንድወሰን። ለትርጉም፡-
ደብሪቱ መርዕድ ካምፖሬያሊ፣
ጋብሪኤላ ጌርማንዲ፣ ኃይሌ ከበደ፣
አንጀሊካ ፔሳሪኒ እና መቅደስ
መስፍን።

### ለህትመት፡-

ይጥና ፍርድይወቅ እና ኤልፊ ጌታቸው
ኑቬሎን።

© 2026 From Oblivion to Memory. መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

# ቀኛዝማች ፀምሩና ቤተሰባቸው

## ቀኛዝማች ፀምሩ ገብረሥላሴ



*ቀኛዝማች ፀምሩ 1960*

ቀኛዝማች ፀምሩ ገብረ ሥላሴ ከእናታቸው ክብርት ወይዘሮ እሴተ እና ከአባታቸው ከክቡር ፀሓፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በ1887 ደብረ ብርሃን ከተማ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም በባሕላዊው የቄስ ትምህርት ገብተው ከተማሩ በኋላ፤ ከወይዘሮ ሠናይት ወልደ ገብርኤል ጋራ ትዳር መሥርተው ዐሥራ ስድስት ልጆችን አፍርተው አሳድገዋል።

ቀኛዝማች ፀምሩ ሀገራቸውን በተለያየ የመንግሥት ኃላፊነት ቦታዎች በብቃት አገልግለው ለአገልግሎታቸው የኒሻን ሽልማቶችን የተቀበሉ ሰው ናቸው። በተለያዩ ጊዜያት በጽሕፈት ሚኒስቴር እና በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ዋና አስተዳዳሪ በመኾን ሠርተዋል። ከዚህ በተጨማሪም በ1913 በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን በሐረርና በወላይታ ነጋድራስ ኾነው አገልግለዋል።



*ቀኛዝማች ፀምሩ 1934*

አስከፊው የአዚናራ ደሴት የእስር ዘመናቸው አብቅቶ ዐዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላም የሐምሌ 16 ኮሚቴ [1] አባል በመኾንም የሠሩ ሲኾን፤ ከዚያም ጡረታ እስከወጡበት ጊዜ ድረስ የሕዝብ ምክር ቤት አባል ኾነው ሕዝባቸውንና ሀገራቸውን አገልግለዋል። ቀኛዝማች ፀምሩ በ77 ዓመት ዕድሜያቸው ከዚህ ዓለም ድካም አርፈው በእንጦጦ ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ቀብራቸው ተፈጽሟል።

## ሻለቃ ጌታብቻ ፀምሩ

ጌታ ብቻ ፀምሩ የቀኛዝማች ፀምሩ የበኩር ልጅ ሲኾኑ አዚናራ ከመታሰራቸው በፊት የሻለቃነት ማዕረግ የተቀበሉ ሰው ናቸው። በታሰሩ ጊዜ ገና ትዳር አልመሠረቱም ነበር ። ጌታ ብቻ አዚናራ በእስር ላይ እያሉ በሕመም ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ሞታቸው ቤተ ሰቡን ለከፍተኛ ሀዘን የዳረገ ሲኾን ሀዘኑን ያከፋው ደግሞ ትዳር ሳይመሠርቱና ዘራቸውን ሳይተኩ በሰው ሀገር መሞታቸው ነው። የሻለቃ ጌታ ብቻ ፀምሩን መሞት ቤተ ሰቡ ያወቀው ወንድማቸው ጥጋሻው በእስር ላይ ኾነው ለወንድማቸው ደበበ ፀምሩ ጽፈው የላኩት ደብዳቤ ላይ የጌታ ብቻ ፊርማ ባለመኖሩ ነበር።

ለዚህ ፅሑፍ ዝግጅት ሲባል በተደረገው ምርምር አዚናራ በእሥር አብረዋቸው የቆዩት ቀኛዝማች ደህኔ ወልደ ማርያም ማስታወሻ ላይ የሚከተለው ቃል ሰፍሯል። "የካቲት 1 ቀን ጌታ ብቻ የሚባል የቀኛዝማች ጻምሩ ገብረ ሥላሴ ልጅ ታሞ ሰንብቶ ስላረፈ የወይዘሮ ሮማን ወርቅ ልጅ ከተቀበረበት ቦታ እዚሁ አዚናራ ተቀበረ። አባ በርሳሊና ባመጡልን ዳዊት ሰባት ቀን ጸሎተ ፍትሐት



ጌታብቻ ፀምሩ

ተደረገለት።" በ2017 አዚናራ ላይ በተደረገው ጉብኝት "ካምፖ ፋሮ" መካነ መቃብር ያረፉት ኢትዮጵያውያን ላረፉበት ቦታ ምንም ምልክት እንዳልተደረገላቸው አስተውለናል። የነበሩት ጥቂት ምልክቶች በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጊዜ ለሞቱ እስረኞች ብቻ የተደረጉ ከመኾናቸው በላይ የመቃብር ቦታው መፈራረስ ላይ ያለና ምንም እንክብካቤ ያልተደረገለት ነው።



አቶ ደበበ የወንድማቸውን ሞት በግምት እንደደረሱበት ለጥጋሻው የገለፁበት ደብዳቤ

## ጥጋሻው ፀምሩ



ኮሎኔል ጥጋሻው ፀምሩ

የቀኛዝማች ፀምሩ ኹለተኛ ልጅ የኾኑት ጥጋሻው ፀምሩ ሐምሌ 6 ቀን 1895 በዐዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። ከወይዘሮ ሮማን መኮንን ጋር በትዳር በኖሩበት ዘመን አራት ልጆችን አፍርተው አሳድገዋል። አዚናራ በእስር ከነበሩበት ተመልሰው የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎችን በመቀላቀል የኮሎኔልነት ማዕረግ ደርሰዋል። በኋላም የሚሊታሪ ዳኛ ኾነው አገልግለዋል። ኮሎኔል ጥጋሻው በ1960ዎቹ ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል።

## እስር በአዚናራ ደሴት



ቀኛዝማች ፀምሩ በአዚናራ 1938

ከየካቲት 12 ጭፍጨፋ ጋር ተያይዞ የጣልያን መንግሥት ቀኛዝማች ፀምሩና ኹለት ልጆቻቸውን ጨምሮ ማኅበረ ሰቡ ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር ዐቅም አላቸው ያላቸውን፣ ሀገራቸውን ከጠላት ወረራ ይከላከላሉ ብሎ የጠረጠራቸውን፣ ትምህርት ወይ ሥልጣን ያላቸውን እና መሰል ሰዎችን በማሰር በመርከብ ወደ አዚናራ ደሴት የወሰዳቸው ሲኾን ከኹለት ዓመት እስር በኋላ ቀኛዝማች ፀምሩ ከአንድ ልጃቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ በቅተዋል።

በዚኽ ወቅት ስለነበረው ኹኔታ ያለው ጥቂት መረጃ የተገኘው ቀኛዝማች ፀምሩ ከባለቤታቸው ወይዘሮ ሠናይት ወልደ ገብርኤል እና ልጃቸው ጥጋሻው ፀምሩ ከወንድም እኅቶቻቸው ጋር ከተጻጻፏቸው ጥቂት ደብዳቤዎች ብቻ ነው። አንዳንድ እስረኞች ኢትዮጵያ ለሚገኙት ቤተ ሰቦቻቸው ፎቶግራፍ መላካቸውን፣እሱንም ተከትሎ የእስረኞቹ ዘመዶች ፎቶግራፎቻቸውን ለማየት እና ስለእነርሱ ዜና ለመስማት እጅጉን መናፈቃቸውን እንዲኹም ካለፈቃዳቸው ከቤተ ሰቦቻቸው ጋራ በመለያየታቸው መጎዳታቸውን ከተላኳኳቸው ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል።

## የመዛግብት ጥናትና ያልተመለሱ ጥያቄዎች



ቀኛዝማች ፀምሩ

የቀኛዝማች ፀምሩን እና ልጆቻቸውን እስር በሚመለከት እስካሁን የተገኙት መረጃዎች ቁንጽል በመኾናቸው፤ ስለእነርሱ መያዝ፣ የእስር ቆይታና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ቤተ ሰቦቻቸው የሚያውቁት ነገር በጣም ጥቂት ነው። በተለይ ስለ ጌታ ብቻ አሟሟትና ቀብር ምንም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ምናልባትም በጣልያን ኾነ በኢትዮጵያ መዛግብት ውስጥ የሚገኝ ዐዲስ መረጃ ካለ ነገሩን ሊቀየረው ይችል ይኾናል ።

## የቤተሰብ ገጠመኝ

ቀኛዝማች ፀምሩና ባለቤታቸው እንጦጦ አካባቢ ቤተሰባቸውን ይዘው ይኖሩ የነበረበትን ትልቅ ባለ ሁለት ፎቅ ቤት አንድ የወራሪው የኢጣልያ ሹም ቀምቷቸው ከነቤተሰቡ ይኖርበት ነበር። በዚህን ጊዜ የኢጣልያዊው አንድ ወንድ ልጅና የሳቸው አንድ ወንድ ልጅ ጓደኝነት መሥርተው በልጅ የዋህነት ጊዜአቸውን አብረው ያሳልፉ ነበር። ከወረራው በኋላ ኢጣልያዊው ቤተሰቡን ይዞ ወደ አገሩ ተመለሰ። ነፍስ ካወቁ በኋላ ኒኒና አልማ የሚባሉ ሁለት የኢጣልያዊው ልጆች ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝት መጥተው በልጅነት የኖሩበትን ቤት ሊያዩ መጥተው ነበር።



አቶ ደበበ ከልጅነት ባልንጀራቸው እና አንድ ማንነታቸው ያልታወቀ እንግዳ ጋር

እዚህ ፎቶ ላይ የሚታዩት የጥጋሻውና የጌታ ብቻ ታናሽ ወንድም የኾኑት አቶ ደበበ ፀምሩ ከእነዚኽ የልጅነት ጓደኞቻቸው ከነበሩ የጣልያን ሹም ልጆች ጋር ተገናኝተው ሳለ ነው። በዚኽ አጋጣሚ አቶ ደበበ በአንድ የባህል ምግብ ቤት ለእንግዶቹ ግሩም መስተንግዶ አድርገውላቸዋል።

---

1 የሐምሌ 16 ኮሚቴ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የልደት በዓል ኮሚቴ ነው።

↑ ወደ ኋላ የተመረጡ ጽሑፎች

# አቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ እና ሥራዎቻቸው



*አቶ መኮንን ወልደዮሐንስ*

አቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ ከእናታቸው ከወይዘሮ ወደርየለሽ ወልደ ገብርኤል እና ከአባታቸው ከአቶ ወልደ ዮሐንስ ናደው በሐምሌ 13 ቀን፣ 1897 በዐዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተወለዱ። እናታቸው ወይዘሮ ወደርየለሽ የመንዝ ተወላጅ ሲኾኑ፣ ዐዲስ አበባ ከተማ አነስተኛ ሱቅ ነበራቸው። አባታቸው አቶ ወልደ ዮሐንስ ናደው ደግሞ ኮርቻ፣ አፎት እና የተለያዩ የቆዳ ምርቶችን በመሥራት የሚታወቁ የቡልጋ ሰው ነበሩ።

አቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ ቀበና አካባቢ በሚገኘው የወላጆቻቸው ቤት ከሦስት ወንድሞቻቸው እና ከአንድ እኅታቸው ጋር የኖሩ ሲኾን፤ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ መጀመሪያ በቄስ ትምህርት ቤት በኋላም ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው በጊዜው በፈረንሳይኛ የሚሰጠውን የሒሳብ እና የሣይንስ ዘመናዊ ትምህርት በጥሩ ኹኔታ ተከታትለዋል። አቶ መኮንን ትጉህና ሥራ ወዳድ በመሆናቸውም በግል የንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው ትልቅ ስኬት አሳይተዋል።

## በወረራው ወቅት

ፋሺስት ጣልያን ሀገራችን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት፤ አቶ መኮንን ወንድማቸው ጸሓፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስን ተከትለው በመዝመት መጋቢት 22 ቀን 1928 በማይጨው ጦርነት ቆስለዋል፡፡ የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎ ወደ ሽምቅ ውጊያ በተዘዋወረበትም ወቅትም እርሳቸው እና ቤተ ሰባቸው ከባድ ዋጋ ለሀገራቸው ከፍለዋል። በዚህ ጊዜ አባታቸው አርበኞችን ረድተዋል በሚል ሰበብ ሲገደሉ፤ ታላቅ ወንድማቸው ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱን ተከትለው ከሀገር ወጥተዋል።

ታዲያ በዚያ አስቸጋሪ ወቅት ወጣቱ አቶ መኮንን የቤተ ሰባቸው ኀላፊ በመኾን ከዕድሜያቸው በላይ የኾነ ከባድ ሸክም ለመቀበል ተገደዋል። ከቤተ ሰብ ኀላፊነታቸው በተጨማሪም የውስጥ አርበኛ በመኾን ሀገራዊ ግዴታቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል፡፡



*አቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ (በስተቀኝ) ከወንድማቸው ከፀሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ ጋር በጦር ሜዳ 1936*

አቶ መኮንን፤ የካቲት 12 ቀን 1929 ግራዚያኒ ላይ በተደረገው የግድያ ሙከራ ሰበብ ታስረው ወደ ጣልያን ሀገር የተወሰዱ ሲኾን፤ መጀመሪያ አዚናራ ከዚያም ሜርኮሊያኖ ካምፕ እስረኛ ኾነው ቆይተዋል። አቶ መኮንን ከእስር ተለቅቀው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ የመጡበትን ትክክለኛ ቀን የሚናገር ማስረጃ ባይገኝም፤ ከድል በፊት በ1931 አብዛኞቹ እስረኞች በተለቀቁበት ወቅት እርሳቸውም ተለቅቀዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

አቶ መኮንን ለቤተ ሰቦቻቸው ተናግረውት እንደነበረው ከኾነ የአዚናራ የእስር ቆይታቸው ለእርሳቸውና አብረዋቸው ለነበሩት ኢትዮጵያውያን እጅግ አስከፊ ነበር፡፡ በዚያ አስከፊ ኹኔታ ውስጥ ኾነው እውቀታቸውን በማሻሻል ጣልያንኛ ቋንቋን ተምረዋል። በተግባረ ዕድ ትምህርት በመሠማራትም የልብስ ስፌት እና የአናጢነት ሙያ ተምረዋል፡፡ በወቅቱ ፋሽስት ጣልያን የአቶ መኮንንን ሙያ በአግባቡ ተጠቅሞበታል፡፡ በልብስ ስፌት ሙያቸው፤ በእርሻ እና በቤት ውስጥ ሥራ አገልግሎት ላይ ለዋሉ እስረኞች የሚኾን የደንብ ልብስ እንዲሰፉ፤ በአናጢነት ሙያቸው ደግሞ ለእስር ቤቱ አገልግሎት የሚውል ወንበር፣ ጠረጴዛ እና የመሳሰሉትን እንዲሠሩ ያደርጋቸው ነበር።

አቶ መኮንን ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር በነበራቸው አለመግባባት ከመንግሥት ሥራ ሲገለሉም፣ የልብስ ስፌት ሙያቸውን በመጠቀም የገዛ ልጆቻቸውን ልብስ በመስፋት ያለብሱ ነበር። የቅርብ ቤተ ሰባቸውንና ነፃነታቸውን ባጡ ሰዐት እንኳን ራሳቸውን ለማሻሻል ወደ ኋላ የማይሉ ብርቱ ሰው ነበሩ።

## የሀገር ግንባታ አስተዋጽኦ

አቶ መኮንን ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ከታላቅ ወንድማቸው ጋር በመኾን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዐዲስ መንግሥት ለማቋቋም የራሳቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ በሙያቸው በቅንነት እና በትጋት ያገለገሉ ሰው ናቸው።

የጦርነቱ ካሣ አፈጻጸም ኀላፊነት ተሰጥቷቸው ከማገልገላቸውም በተጨማሪ፤ አቶ መኮንን ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ የኾነውን የአባ ሳሙኤል ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኀይል ማመንጫ ተቋም እድሳት አካሂደው፤ በተጨማሪነትም ዐዳዲስ ተርባይኖች እንዲገጠሙ በማድረግ የኤሌክትሪክ ኃይል ስርጭት እንዲስፋፋ አድርገዋል። ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ባለሥልጣን ሲቋቋም

በሥራ አስኪያጅነት በመምራት፤ መኻል አዲስ አበባ ፒያሳ ላይ ለድርጅቱ ግዙፍ ሕንጻ አስገንብተዋል፡፡ ይኽ ታሪካዊ ሕንጻ አኹንም ድረስ ለገነቡት ተቋም ሕያው ምስክር ኾኖ ይታያል።



*ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት (በስተቀኝ) እና አቶ መኮንን በስተግራ የአባ ሳሙኤል ተርባይኖች ምረቃ ላይ 1935 ገደማ*

አቶ መኮንን ለኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የኾነውን አንበሳ አውቶቡስንም ለመመሥረት ተግተው ከሠሩት ወገኖች መኻል አንዱ በመኾን፤ ሕዝብን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በትራንስፖርት በማጓጓዝ እና ከተማን በማዘመን ሂደት ላይ የራሳቸውን አሻራ ያሳረፉ ታላቅ ሰው ናቸው።

አቶ መኮንን፤ ከዘመን ተጋሪዎቻቸው ጋራ በመኾን ሀገራቸውን ከጦርነት እና ከወረራ እንድታገግም ለማድረግና ለመለወጥ ትልቅ ራዕይ ነበራቸው፡፡ ከ1940ዎቹ መጨረሻ እስከ 50ዎቹ መጀመሪያ የሀገራቸውን ግንባታ በትጋት ሲከታተሉና ሲያካሄዱ ከቆዩ በኋላ፤ በጊዜው በተፈጠሩ አንዳንድ የፖሊቲካ ውጥረቶች መካከል እክል ገጥሟቸው፤ እርሳቸውና ተፅዕኖ ፈጣሪው ወንድማቸው ጸሓፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ላይ ሹም ሽር ተካሄዷል። በዚህም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ለዐሥራ አምስት ዓመታት በግዞት ታስረው ኖረዋል።



*አቶ መኮንን (ወረቀት ይዘው የሚያነብቡት) የመጀመሪያው ሥራ አስኪያጅ ሆነው ባገለገሉበት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ባለሥልጣን ፅሕፈት ቤት ሆነው በ1940 ገደማ*

## የግል ሕይወት

አቶ መኮንን ወይዘሮ ቆንጂት ዘውገን አግብተው ዐሥር ልጆችን ወልደው አሳድገዋል። በስተርጅና ዘመናቸውም ከሃያ የልጅ ልጆቻቸው ጋር ለሚያሳልፉት ጊዜ እጅግ ትልቅ ዋጋ ይሰጡ ነበር። የቤታቸውም አስተዳደር ልክ እንደ ሥራቸው፤ ትጋት፣ ጽናት እና ፍቅር፣ ይንፀባረቅበት ነበር።

አቶ መኮንን ከመንግሥት ሥራ ከተገለሉ በኋላ እጃቸውን አጣምረው የተቀመጡ ሰው አልነበሩም። ዐዲስ አበባ ውስጥ የከብት እርባታ ከመጀመራቸውም በላይ ከአዚናራ እስር ቤት በቀሰሙት ሙያ ዕድሜ ልካቸውን የተዋጣላቸው ግንበኛ እና አናጢ በመኾን ቤታቸውን እና አካባቢያቸውን በአግባቡ የተንከባከቡ ሰው ነበሩ።

አቶ መኮንን ወልደ ዮሐንስ በ85 ዓመት ዕድሜያቸው ታኅሣስ 20 ቀን 1983 ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ተለይተው ሥርዐተ ቀብራቸው በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል።

## ቅርስ

አቶ መኮንን ሀብተወልድ፤ ከቄስ ትምህርት ቤት እስከ ጦር ሜዳ፣ ከባዕድ ሀገር የእስር ቤት ቆይታና የብቸኝነት ጊዜ እስከ ታላላቅ የመንግሥት ሥራ ኀላፊ በመኾን ሀገር በማቅናት፤ ከዚያም ሲቀጥል በጡረታ ዕድሜያቸው ቤት እና አካባቢን በመገንባት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ ብርቱ ሰው ናቸው። በሥራ ዘመናቸውም ያተረፉት እውቅና ከትህትናቸው እና ከትጋታቸው የመጣ እንጂ በሥልጣንና ማዕረጋቸው ያገኙት አልነበረም። ለሀገራቸው ኢትዮጵያ እንዲኹም ለቤተ ሰባቸው ባደረጉት ጉልህ አስተዋጽኦ ከአባ ሳሙኤል ተርባይኖች ጀምሮ እስከ አንበሳ አውቶብስ ድርጅት፤ ከግዙፉና ታሪካዊው የመብራት ኃይል ሕንጻ እስከ መኖርያ ቤታቸውና አከባቢያቸው ድረስ አሻራቸውን ያስቀመጡ ትውልድ የሚዘክራቸው ታላቅ ሰው ናቸው።



*አቶ መኮንን ወልደዮሐንስ 1970*

↑ ወደ ኋላ የተመረጡ ጽሑፎች

# አሜሪካን ግቢ



*መርካቶ የሚገኘው አሜሪካን ግቢ።*

በ1910 አጋማሽ፣ በዘመነ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፣ መርካቶ አካባቢ አንድ የድንጋይ ሕንጻ ተገነባ። ሕንጻው የተገነባው በወቅቱ የጦር ሚኒስትር ለነበሩት ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ መኖርያ እንዲኾን ታስቦ ነው። የጦር ሚኒስትሩ ወደዚኽ መኖርያ ቤት ከመዘዋወራቸው በፊት አሁን የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የቆመበት ስፍራ[i] ላይ የተሠራ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። የእርሳቸው አጃቢዎችም እዚያው አካባቢ ይኖሩ ስለነበረ መርካቶ ዙሪያ ሰፊ መሬትና ንብረት ነበራቸው። በርግጥ ያ በድንጋይ የተሠራና ግርማ ሞገስ ያለው ሕንጻ መኖሪያ ቤታቸው ብቻ ሳይኾን፤ ችሎት ማስቻያቸውም ነው።

ሕንጻው ከተገነባ ከኹለት ዐሠርት ዓመታት በኋላ ከወርኀ መስከረም ከ1928 ጀምሮ እስከ ጣሊያን ወረራ ፍጻሜ ድረስ፤ “በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር” በቀደሞው አጠራሩ “በኢትዮጵያ ነዋሪ የአሜሪካ ሚኒስትር” የነበሩት የኮርኔሊየስ ቫን ኤንግርት[ii] መኖርያ ቤት እና ፤ የአሜሪካን ቆንስላ ጽሕፈት ቤት በመኾን አገልግሏል። ይኽ ሕንጻ የአሜሪካን አምባሳደር መኖሪያ እና የአሜሪካን ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ኾኖ በማገልገሉ የተነሳ “አሜሪካን ግቢ” የሚል ተለምዷዊ ስያሜ አገኘ። ይኽ ስያሜ የአካባቢውም መጠሪያ በመኾን እስካኹን ድረስ እያገለገለ ይገኛል።



*አሜሪካን ግቢ ውስጥ መሸሸጊያ ሆኖ ያገለገለው ቤት።*

በየካቲት 12 ቀን 1929፤ ፋሺስት ጣሊያን “የጣሊያን ምሥራቅ አፍሪካ” ብላ ለሰየመችው ግዛት እንደራሴ የነበረው ማርሻል ሮዶልፎ ግራዚያኒ ላይ የተደረገውን የግድያ ሙከራ ተከትሎ፤ በዐዲስ አበባ ውስጥ ለሦስት ቀናት የቆየ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ተካሄደ።[iii] በዚህ ወቅት “ጥቁር ሸሚዝ” (Black Shirts) በመባል የሚታወቁት የፋሺስት ጣሊያን ሚሊሻዎች፣ መደበኛ ወታደሮች እና ካራቢኔሬ (ፖሊሶች) በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን በአሰቃቂ ኹኔታ ጨፈጨፉ።[iv]

በነዚያ የጭንቅ ቀናት፤ በአሜሪካን ግቢ አቅራቢያ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን ለማትረፍ ወደ “አሜሪካን ግቢ” (የአሜሪካን አምባሳደር መኖሪያ እና የአሜሪካን ቆንስላ ጽሕፈት ቤት) ሸሹ። አምባሳደር ኮርኔሊየስ ኤንግርትም ኹለቴ ማሰብ ሳያስፈልጋቸው ሕይወታቸውን ለማትረፍ የመጡትን ኢትዮጵያውያን አስጠልለዋቸዋል። በወቅቱ በተደረገው ቆጠራ መሠረት፣ ከየካቲት 12 እስከ 16 ባሉት ቀናት ውስጥ ወደ 700 ኢትዮጵያውያን በ“አሜሪካን ግቢ” ውስጥ ተጠልለው ነበር። ከእነዚኽም መካከል 248 ወንዶች፣ 262 ሴቶች እና 195 ሕፃናት ነበሩ።[v]

## የአምባሳደሩ ጠንካራ አቋም

የካቲት 16 ቀን 1929 የአሜሪካው የውጪ ጉዳይ ሚኒስተር ለኤንግርት በላኩት የቴሌግራም መልዕክት፤ መሥሪያ ቤቱ በአካባቢው ለነበሩ ኢትዮጵያውያን መጠለያ መስጠቱን ከሰብአዊነት አንጻር መቀበሉን፤ ነገር ግን የኢትዮጵያውያኑ እዚያ መገኘት በአምባሳደሩ እና በሠራተኞቻቸው ላይ አደጋ ሊያስከትል ስለሚችል፤ በዚያ የተጠለሉት ኢትዮጵያዊያንን ሕይወት ለአደጋ በማያጋልጥ መልኩ ከግቢው ለማስወጣት ዝግጅት እንዲያደርጉ መከሯቸው።[vi] አምባሳደር ኤንግርት ግን በግቢው ለተጠለሉት ኢትዮጵያዊያን ደኅንነት ቅድሚያ በመስጠት፤ ከጣሊያን ባለሥልጣናት ዋስትና ሳያገኙ ኢትዮጵያዊያኑን ከግቢው ማስወጣት አልፈቀዱም።[vii]



*አምባሳደር ኮርኒሊየስ ኤንገርት*

እነዚያ በሕንፃው ውስጥ ተጠልለው ሞትን ያመለጡ ኢትዮጵያዊያን መውጣት የጀመሩት፤ ኤንግርት ከጣሊያን ባለሥልጣናት ዋስትና ካገኙ በኋላ ነበር። ጭፍጨፋው ከተጀመረ ከስድስት ቀናት በኋላ በየካቲት 19 ቀን ኢትዮጵያውያኑ ግቢውን ለቅቀው ወጡ።[viii] ግቢውን ለቅቀው ከወጡ በኋላ የሰዎቹን ዕጣ ፈንታ በሚመለከት፤ የአሜሪካው አምባሳደር ለውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤቱ ምንም ጉዳት አልደረሰባቸውም ቢሉም፤ የእንግሊዝ ፓርላማ አባል የዓይን እማኞችን ቃል መሠረት በማድረግ ከግቢው ሲወጡ ጥቃት እንደተፈጸመባቸው ለፓርላማው ሪፖርት እንዳደረጉ ኢያን ካምፕቤል በመጽሐፉ ገልጿል።[ix]

"አሜሪካን ግቢ" ከነፃነት በኋላ በኢትዮጵያ ለሚኖሩ የየመን ማኅበረ ሰብ አባላት እንደ ትምህርት ቤት ሆኖ እንዲያገለግል ተሰጥቷል። የመናውያኑም ከ70 ዓመታት በላይ ሲገለገሉበት ቆይተዋል። ታሪክ የሚያስበው ይገኝ እንጂ ተዳፍኖ አይቀርምና ከጭፍጨፋው 84 ዓመታት በኋላ፣ እ.ኤ.አ. በ2021 በዐዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካን ኤምባሲ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል፤ ታሪካዊ ሕንጻዎች እንዳይፈርሱና ተጠብቀው እንዲቆዩ በመሚገት የሚታወቀውን፣ "ሄሪቴጅ ዎች ኢትዮጵያ" የተሰኘ ሀገር በቀል ድርጅትን በመቅጠር፤ በግቢው ውስጥ ተጠልለው የነበሩ ሰባት መቶ ሰዎች መጨረሻ ምን እንደኾነ እንዲያጠናለትና፤ ከተገኙም የልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸው ምስክርነት እንዲሰንድለት ይጠይቃል።[x]

## የተረፉትን ፍለጋ



*በዝግጅቱ ታድመው የነበሩ ተወላጆች*



*አቶ ምትኩ ገብረ ሚካኤል*

ከጭፍጨፋው የተረፉትን ኢትዮጵያውያን፤ ቤተ ሰቦች፣ ልጆች እና የልጅ ልጆች ለማግኘት የተደረገው ጥረት ከመጀመሪያው ጀምሮ ፈታኝ ነበር። ኾኖም ጉዳዩን የያዙት ሰዎች እንደ ሰንበቴ ማኅበር ባሉ ሃይማኖታዊ አደረጃጀቶች ላይ ትኩረት በማድረጋቸው የማታ ማታ ለውጤት አብቅቷቸዋል። በአንዱ ሰንበቴ ማኅበር አማካኝነት ቡድኑ የመጀመሪያ የመረጃ ምንጩ የኾኑትን አቶ ምትኩ ገብረሚካኤልን አገኘ። እርሳቸውም የተጠቆሙት በእኅታቸው በወይዘሮ ሳካምየለሽ ገብረሚካኤል በኩል ሲኾን አባታቸው በደብረ አሚን ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው የታላቁ የሰንበቴ ማኅበር መሥራች ሲኾኑ እርሳቸውም አባታቸውን ተክተው የሰንበቴው አባል ናቸው።

አቶ ምትኩ ወላጆቻቸው በ"አሜሪካን ግቢ" አቅራቢያ ይኖሩ የነበሩ ሦስት ግለ ሰቦችን ስም አስታውሰው ከእነአድራሻቸው ለአጥኚው ቡድን ሰጡ። ቡድኑም ከተጠቆሙት ሰዎች መካከል አቶ ታዬ የተባሉትን ሰው ሲያናግር፤ አባታቸው አቶ ገብረሚካኤል ገብርዬ እና እናታቸው ወይዘሮ ዓለሚቱ ገብሩ በቆንስላው ጽሕፈት ቤት ውስጥ ተጠልለው ሕይወታቸውን እንዳተረፉ አረጋገጡ። ስማቸውም በግቢው ውስጥ በተጠለሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ተራ ቁጥር 99 ላይ ተገኘ። በተጨማሪም ተመራማሪዎቹ በተራ ቁጥር 100 ላይ ተመዝግበው የሚገኙትን የአቶ ተገኘ እምሩ እና የባለቤታቸው የወይዘሮ ወሰኔ አቦዬን ልጅ እና የልጅ ልጆች ማግኘት ቻሉ።[xi]

የካቲት 15 ቀን 2014 የአሜሪካን ኤምባሲ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል በግቢው ውስጥ ልዩ የሕዝብ መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። በመድረኩ ላይ ታዋቂው አርክቴክት ፋሲል ጊዮርጊስ የሕንጻውን ታሪክ፣ ኢያን ካምቤል የኤንግርትን ጀግንነት፣ እና “የሄሪቴጅ ዎች ኢትዮጵያ” ዳይሬክተር ልዕልት አስቴር አንቶሒን ደግሞ የምርምር ውጤቱን አቅርበዋል። በዕለቱም ከ85 ዓመታት በፊት የወላጆቻቸው ሕይወት በተረፉበት በዚያው ሕንጻ ውስጥ ከጭፍጨፋው የተረፉት ኢትዮጵያውያን ልጆች እና የልጅ ልጆች እንዲገኙ ተደርጓል።[xii]



*ጥናቱን ያካሄዱት ሰዎች*

## ማጣቀሻዎች

[i] ይህ መረጃ የተገኘው ለሁለት ዓመት ተኩል ሕንፃውን አድሶ የማቆየት ኃላፊነት ወስደው ከሠሩት ፍቅረሥላሴ ስፍር ከተባሉት ታሪካዊ ቦታዎችን በማስጠበቅ ከሚታወቁት አርኪቴክት ነው።

[ii] The Saved 700. (2023, July). State Magazine. https://statemag.state.gov/2023/07/0723feat04/

[iii] እንግሊዛዊው የታሪክ ተመራማሪ ኢያን ካምቤል፤ የየካቲት ዐሥራ ኹለቱን አሰቃቂ ጭፍጨፋ. የተመለከቱ አራት የተዋጣላቸው መጻሕፍትን አሳትመዋል። እነዚህም መጻሕፍት፤ "The Plot to Kill Graziani" (2010) (የግድያውን ሙከራ ሙሉ ታሪክ የሚተነትን) ፤ "The Massacre of Debre Libanos" (2014) (በሺዎች የሚቆጠሩ መነኰሳት፣ ቀሳውስት እና ዲያቆናት የተረሸኑበትን ኹኔታ በዝርዝር የሚያብራራ) ፤ "The Addis Ababa Massacre" (2017) (በመዲናዋ ለሦስት ቀናት የተካሄደውን የንጹሐን ዜጎች ጭፍጨፋ የሚተነትን) እና "Holy War" (2021) (በጣሊያን ወረራ ወቅት የቫቲካንን ዐቋም ምን እንደነበር የሚያሳይ) ይሰኛሉ።

[iv] አምባሳደር እምሩ ዘለቀ ሰኔ 24 ቀን 2014 ከሄሪቴጅ ዎች ኢትዮጵያ ጋር ባካሄዱት ቃለ ምልልስ ያንን ዘግናኝ የጭፍጨፋ ወቅት አስታውሰዋል። ፋሺስት ጣሊያኖች ዕድሜም ኾነ ጾታ ሳይለዩ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንን ለመግደል ጠብመንጃ፣ ሳንጃ፣ ቢላዋ፣ አልፎ ተርፎም ዶማና አካፋ ሲጠቀሙ በዐይናቸው መመልከታቸውን አምባሳደሩ ተናግረዋል። በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በ2016 በታተመው “A Journey: Memoirs” በሚለው የግል ማስታወሻቸው ገጽ 29 ላይ ይህንኑ ሐሳብ አስፍረዋል።

[v] U.S. Department of State. (1954). Foreign relations of the United States, 1937 (Vol. 2). p. 682 & 684

## [vi] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 686

## [vii] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 682

## [viii] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 684

[ix] Campbell, Ian. (2017). The Addis Ababa massacre: Italy's national shame. Oxford University Press. p. 235.

[x] The Saved 700. (2023, July). State Magazine. https://statemag.state.gov/2023/07/0723feat04/

[xi] Heritage Watch Ethiopia. (2023). Revisiting narratives of Yekatit 12, 1937

[xii] The Saved 700. (2023, July). State Magazine. https://statemag.state.gov/2023/07/0723feat04/

## ምንጮች

Ian Campbell. (2017). The Addis Ababa massacre: Italy's national shame. Oxford University Press.

Imru Zelleke (2016). A journey: Memoirs. CreateSpace Independent Publishing Platform.

Heritage Watch Ethiopia. (2023, March 20). Revisiting narratives of Yekatit 12, 1937: In search of survivors at the American Gibbi (Unpublished report).

U.S. Department of State. (2023, July). Saved 700: Remembering a heroic act in Addis Ababa. State Magazine. https://statemag.state.gov/2023/07/0723feat04/

U.S. Department of State. (1954). Foreign relations of the United States diplomatic papers, 1937: The British Commonwealth, Europe, Near East and Africa (Vol. 2). U.S. Government Printing Office.

↑ ወደ ኋላ የተመረጡ ጽሑፎች